በልደታ ክፍል ከተማ የተሰፋ ኮከብ ጉድኝት ማዕከል የ 2015 ዓ.ም የመጀመርያ መንፈቀ ዓመትየ 8 ኛ ክፍል የአማርኛ ሞዴል ፈተና

መመርያ አንድ ፦ ከጥያቄ ቁጥ አንድ አስር ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሰረቱ ናቸው ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ

<u>ምንባብ</u>

ከአንድ ምዕተ ዓመት በፊት በህዳር ወር ውስጥ መላ ሃገሪቱን ያደረሰ ወረርሽኝ ተስፋፍቶ ነበር ። ይህ በሽታየህዳር በሽታ ተብሎ ይነገራል። በሽታው ቤተመንግስቱንም ተዳፍሮ ኖሮ የወቅቱ መኳንንትና መሳፍንት በጠና ይታመማሉ በሽታ እንደሚከላከል ስለሚታመንበት በመላው ሀገሪቱ በተለይም በአዲስ አበባ ሁሉም የአካባቢውን ቆሻሻ ሰብስቦ ያቃጥላል

ምናልባት ከዛሬ መቶ ዓመት በፊት በአዲስ አበባ እና በዙሪያዋ የሚፈጥረው ቆሻሻ የእርሻ ቃርሚያ ከከብቶች አዛባ እና ከሰዎች አይነምድራቸው በየቦታው ከመፀዳዳት ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል ። እንዚህ ተሰብስበው ቢቃጠሉ ጉዳት አያኖራቸውም ባይባልም የዛሬው ቆሻሻ ግን በመጠኑ በይዘቱም ይለያል ። ዛሬ በደረቅ ቆሻሻነት የሚፈጠረው ውጋጅ ፕላስቲክ የተለያዩ ብረቶች ተፈጥሮአዊ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን ሲቴቲክ የያዘ ነው ።

ሲቀጥልም አደገኛ እና መርዘኛ የሆኑ ንጥረ ነገር ይፈጥራሉ ። በአዲስ አበባ ከተማ በቀን 2256 ሜትር ኩብ በላይ ደረቅ ቆሻሻ ይፈጠራል ። ከዚህም ቆሻሻ ውስጥ ከ 60 -70% የሚሆነው ብቻ እንደሚሰበሰብ እና እንደሚወገድ ይታመናል ።

የነፍስ ወከፍ የቀን ቆሻሻ መጠን ከ 300-400 ግራም በክረምት ወራት እንዲሁም ከ 160- 250 ግራም በደረቅ ወራት እንደሚሆን ይገመታል ።

ከመኖርያ ቤት የሚመነጨው ቆሻሻ ሲቃጠል የሚወጣው ጭስ አየርን የመመረዝ ለብክለት መንሰዔ ይሆናል ይህ ደግሞ በጤና ላይ ጉዳት ያደርሳል ። ብሎም ለካንሰር ያጋልጣል ።

በተጨማሪም ቆሻሻው በሚቃጠልበት ጊዜ በጭስ አማካኝነት ለችግሩ ዋነኛ ምንጭ የሆኑት መርዘኛ እና አደገኛ የሆኑ ውህዶች ይፈጠራሉ ። እነዚህ አደገኛ ውህዶች ደግሞ ለመተንፈሻ አካል መታወክ የሰውነት በሽታን የመከላከል ስርዓት ላይ ጫና በማሳደር የተለያዩ ካንሰር በሽታዎችን የሚያስከትሉ ናቸው።

አ.አ.አ ጥ. ባለስልጣን

ተሻሽሎ የቀረበ

1. አሁን እየተፈጠር ያለው ቆሻሻ ከድሮው ጋር ሲነፃፀር ልዩ የሚያደርገው ከሚከተሉት አማራጮች የትኛው ነው
   ሀ/ ተፈጥሯዊ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን መያዝ
   ለ/ ተሰብስቦ ሲቃጠል ጉዳት የሚያደርስ መሆኑ
   ሐ/ በቀላ ሊወገድ የሚችል መሆኑ
   መ/ አደገኛ እን መዘዘኛ የሆነ ንጥረ ነገር የማይፈጥር መሆን

2. የምንባቡ ሶስተኛ አንቀስ ለምን እንደሚናገር የሚያመለክተው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው

ሀ/ የቆሻሻ መቃጠል በንብረት ላይ አደጋ ማድረስ

ለ/ ከመኖርያ ቤቶች ስለሚሰበሰበው ቆሻሻ ብዛት

ሐ/ በቆሻሻ መቃጠል ምክንያት በሰዎች ጤና ላይ ስለሚደርሰው ጉዳት

መ/ ቆሻሻ በሚቃጠልበት ግዜ ስለሚደረገው ጥንቃቄ

3. ስለሀዳር መታጠን ታሪካዊ አመጣጥ የሚገልፀው አንቀፅ ስንተኛው ነው

ሀ/ አንደኛው ለ/ ሁለተኛው ሐ/ ሶስተኛው መ/ አልተገለፀም

4. መላ ሀገሪቱ ያዳረሰ <u>ወረርሽኝ</u> ተከስቶ ነበር በሚለው ዓ. ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ትርጉም ከሚከተሉት አማራጮች የተኛው ነው

ሀ/ጦርነት ለ/ ከበባ ሐ/ ተስቦ መ/ ዘረፋ

5. በአዲስ አበባ ከተማ ከሚፈጠር ቆሻሻ ተስብስቦ የሚወገደው በመቶኛ ሲታሰብ ምን ያህል እንደሆነ በሚያመለክተው አማራጭ የትኛው ነው

ሀ/ ከ 40-50 % ለ/ ከ 70-80 % ሐ/ከ 60-70 % መ/ ከ 80-90 %

6. በሁለተኛው አንቀፅ ሁለተኛው ዓ.ነገር መጀመርያ የሆነው «እንዚህ» የሚለው ቃል የሚጠቀሰው ከሚከተሉት አማራጮች የትኛው ነው

ሀ/ ቆሻሻ ፣ብናኝ ፣መፀዳዳት ሐ/ ቃርሚያ ፣አዛባ ፣አይነ-ምድር

ለ/ ሰዎች ፣አዲስ ከተማ ፣ብክለት መ/ ካርቦን ዳይኦክሳይድ ፣ናይትሮን ፣ኦክሳይድ

7. ---------- የሚፈጠረው ቆሻሻ ከእርሻ ቃርሚያ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል

ሀ/ ከአጨዳው በኋላ የተሰበሰበ ገለባ

ለ/ ከአጨዳ በኋላ የተሰበሰበ የእህል ዛላ

ሐ/ ከአጨዳ በኋላ የተሰበሰበ ወደ ጎተራ የሚገባ ምርት

መ/ ከአጨዳ በኋላ የተሰበሰበ ሳር ወይም ድርቆሽ

8. በምንባብ መልክ የቀረበው ፅሁፍ የህዳራ መታጠንን የቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት

ሀ/ ይቃወማል ለ/ ያበረታታል ሐ/ ይደግፋል መ/ ያጠናክራል

9. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል በአዲስ አበባ ስለሚፈጠረው የነፍስ ወከፍ ቆሻሻ ትክክለኛ ሀይለቃል የያዘው የትኛው ነው

ሀ/ የነፍስ ወከፍ የቀን ቆሻሻ መጠን ከክረምት ወራት ይልቅ በበጋው ወራት ይበልጣል

ለ/ የነፍስ ወከፍከቀን ቆሻሻ መጠን በክረምት በበጋው እኩል መጠን አላቻው

ሐ/ የነፍስ ወከፍቆሻሻ በክረምት በበጋም ግምቱ አይታወቅም

መ/ የነፍስ ወከፍየቀን ቆሻሻ ከበጋው ይልቅ በክረምት ወራት ይበዛል የምን

10. በምንባቡ ዕርዕስ ምን ይመስላችኋል ከተሰጡት አማራጮች ይበልጥ የሚቀርበውን ምረጡ

ሀ/ ወረርሽ በሽታ ለ/ ቆሻሻ ማቃጠል ሐ/ ህዳር ሲታጠን መ/ የቆሻሻ ክምርት

መመርያ ሁለት ፡- ከተራ 11 እስከ 51 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል ለእያንዳንዱ ጥያቄ በአጠያየቁ መሰረት ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ጪ

11. አንድ ድርሰት ለመፃፍ ትክክለኛ የሆነው ቅድመ ተከተል የቱ ነው

ሀ/ አስተዋፁዎ መንደፍ፣ እርስ መምረጥ ፣እረቂቅ መፃፍ ፣ፅሁፍን ማረም

ለ/ እርስ መምረጥ፣ አስተዋፁዎ መንደፍ ፣እረቂቅ መፃፍ ፣ፅሁፍን ማረም

ሐ/ እርስ መምረጥ ፣አስተዋፁዎ መንደፍ ፣ ፅሁፍን ማረም ፣እረቂቅ መፃፍ

መ/ እረቂቅ መፃፍ ፣ እርስ መምረጥ ፣አስተዋፁዎ መንደፍ፣ ፅሁፍን ማረም

12. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ብዛትን የሚያመለክት ቅጥያ የያዘው ቃል የቱ ነው

ሀ/ ልጆቻቸው ለ/ መስዕቦቻቸው ሐ/ ሳር ቤታቸው መ/ ትምህርት ቤታቸው

13. አንድ ተናጋሪ ለአንድማጮች ሀሳብን በንግግር ለማቅረብ ሲያስብ ከሁሉም አስቀድሞ ማከናወን የሚጠበቅበት ምንድን ነው

ሀ/ ሌላሰው እንዲናገር ማድረግ ለ/ የሚናገርበትን ዕርስ መምረጥ

ሐ/ አድማጮችን ማመስገን መ/ ለዝግጅት ማቅረብ

14. ከሚከተሉት ውስጥ ግሳዊ ሀረግ የሆነው የቱ ነው
ሀ/ ወደቤት የመጣ ልጅ ቶሎ ለ/ ወ/ሮ ሳራ እንደልጅዋ ክፉኛ
ሐ/ ትናትና የመጣው መኪና መ/ ትናትና ወደ ት/ቤት ሄደ
15. ስርዓተ- ነጥቦች ለምንይጠቅማሉ
ሀ/ ስርዓተ-ፅሁፋችንን በአግባቡ ለማከናወን ለ/ አንድ ፅሁፍ ዬዘውን ሀሳብ በትክክል ማስተላለፍ እንድንችል
ሐ/ ብዙም ጠቀሜታ የላቸውም መ/ ሀእና ለ መልስ ናቸው
16. ድርሰተ ከመግፋችን በፊት ዋና ዋና ነጥብን የምናስቀምጥበት ክፍል ---------- ያባላል
ሀ/ መግቢያ ለ/ ሀተታ ሐ/ ቢጋር መ/ ውህደት
17. ከሚከተሉት ውስጥ ላልቶና ጠብቆ ሲነበብ የተለያየ ትርጉም የሚሠጠው ቃል የቱ ነው
ሀ/ ትንታ ለ/ በሽታ ሐ/ ጉምጉምታ መ/ ዱታ
18. የተዋስኩትን መፅሐፍ <u>በማግስቱ</u> እንደመልስ ጠይቆኝ ነበር ።በሚለው ዓርፍት-ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል የምን ተውሳከ ግስ ነው?
ሀ/ የጊዜ ለ/ የቦታ ሐ/ የሁኔታ መ/ የአላማ
19. «ውሽታም » በሚለው ቃል ውስጥ ያለው ትርጉም ለወጨጫ ቅጥያ ---------- ነው
ሀ/ -ም ለ/-ታ ሐ/ -አም መ/ ውሽት
20. የሁለት ነገሮች ጥቅማቸውንና ጉዳታቸውን የሚያነፃጽር የድርሰት ዓይነት ---------- ይባላል
ሀ/ ገላጭ ድርሰት ለ/ ተራኪ ድርሰት ሐ/ አመዛዛኝ (አወዳዳሪ) ድርሰት መ/ ስዕላዊ ድርሰት
21. ከሚከተሉት ዓርፍተ ነገሮች መካከል ስለ አጭር ልብወለድ ትክክል የሆነው የቱ ነው
ሀ/ አጭር ልብወለድ ገጸባህሪያት በታሪክ ውስጥ በረካታ ግጭቶች ይገጥማቸዋል
ለ/ አጭር ልበወለድ ደራሲ የራሱን ፍልስፍና ዘርዘር አድርጎ እንደሚያቀርብ ያስችለዋል
ሐ/ አጭር ልብወለድ የረዣዥም ልበወለድ ቅንጫቢ ሊሆን ይችላል
መ/ አጭር ልብወለድ ጭብጥ ነጠላ ወይም አንድ ነው
22. ከሚከተሉት ውስጥ የአማረኛ ብዙ ቁጥር አመልካቾች ቅጥያ የሆነው ------- ነው
ሀ/አች ለ/ ኣችን ሐ/ ኣችው መ/ አቻቸው
23. ጤነኝነት ካላልተሰማኝ አካባቢዬ ወደሚገኘው ጤና ጣቢያ ሄጀ ስመረመር የሳንባ ነቀርሳ እንዳለብኝ ተነገረኝ ህክምናውን መከታተል ጀመርኩ ---------እንደበፊቱ ተሯሩጬ መስራት አልቻልኩም ------ ከሳንባዬ እመም ባገግምም የሌሎች በሽታዎች ስሜት ይታይብኝ ነበር ። በክፍት ቦታዎች መግባት ያለባቸው አያያዣች በቅድም ተከተል የትኞቹ ናቸው ?

ሀ/ ምክንየቱም ነገር ግን ለ/ ስለዚህ ነገር ግን ሐ/ ሆኖም ፣ስለዚህ መ/ ነገር ግን ፣ምክንያቱም

24. (ዋልጌ) ለሚለው ቃል አቻፍቺው --------- ነው።
ሀ/ ወሽካታ ለ/ ለፍላፊ ሐ/ ባለጌ መ/ ክፈፋ
25. አቶ ከበደ <u>የውሃ ሽታ</u> ሆኑ የተሰመረበት ፈልጣዊ ቃል ፍቺ ---------- ነው

ሀ/ሽታው የማይታወቅ ለ/ ደብዛው ጣፍ ሐ/ ኩልል ያለ ውሃ መ/ ተንኮለኛ

26. ---------- ራሳቸውን ችለው የማይቆሙ የድምጾች ስብስብ ሲሆኑ ከነዓ ምዕላዶች ጋር ወ.ዘ.ተ ለውጥን ያመጣል ።
ሀ/ ነዓ ምዕላድ ለ/ ጥገኛ ምዕላድ ሐ/ ምዕላድ መ/ ቅንጣት
27. በእለት ተዕለት ኑራችን የምንጠቀመው ቃል ---------- ይባላል
ሀ/ ተዘውታ ቃል ለ/ ድርብ ቃል ሐ/ ኢተዘውታሪ ቃል መ/ ሁሉም መልስ ነው
28. «ልላእልሽ እንዴ መቀስ እርሜዶ አልተጫነሽ እደሁ---------» በሚለው የሀዘን ቃላዊ ግዚም ውስጥ የሁለተኛ ስንኝ መዳረሻ ሀረግ የሚሆነው---------- ነው
ሀ/ ግርግዳው ተንዶ ለ/ አፈሩ ተንዶ ሐ/ አልጋው ተንገዳግዶ መ/ ተምዘግዝቶ
29. ከሚከተሉት ውስጥ የረጅም ልቦለድ ባህሪ ያልሆነው የቱ ነው
ሀ/ ቁጥብነት ለ/ ጥድፊያ ሐ/ ነጠላ ውጤት መ/ ሁሉም መልስ ነው
30. የአንቀፅን ዋና ሀሳብ የሚይዘው ክፍል ---------- ይባላል
ሀ/ ሀይል ቃል ለ/ መዘርዘር ዓ/ነገር ሐ/ ተራኪ መ/ ውህደት

31. ገና በወጣትነቱ <u>መክሊቱን</u> አገኘ ። በሚለው ዓ.ነገር የተሰመረበት ቃል ትርጉም ምን ማለት ነው ።

ሀ/ ስልጣን ለ/ ተሰጦ ሐ/ እውቀት መ/ ሽልማት

32. «ልግመኛ »ለሚለው ቃል ተቃራኒ ፍቺ የቱ ነው

ሀ/ ታታሪ ለ/ አልምጥ ሐ/ ደፋር መ/ ሰነፍ

33. ለሙዚቃ ያለኝ ፍቅር ልክ የለውም ፣ለድራማ ግን እስከዚህም ነኝ።

የተሰመረበት ሀረግ ፍቺ የያዘው የትኛው ነው

ሀ/ የድራማ ፍቅር የለኝም ለ/ የድራማ ፍቅር ውስን የለመው ሐ/ የድራማ ፍቅር እንደሙዚቃ አይሆንም መ/ ለድራማ ግድ የለኝም

34. ባልቻ የንግድ ስራውን ለማስፋፋት ቢፈልግም <u>ወረት</u> አነሰው በዚህ ዓ.ነገር ውስጥ የተሰመረበትን ቃል ሊተካ የሚችለው ቃል የቱ ነው ?

ሀ/ አፋላ ለ/ ወቅታዊ ሐ/ ሀብት መ/ ገንዘብ

35. ከሚከተሉት ውስጥ የአንቀፅ ባህሪ ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ/ ገንቢነት ለ/ አፅንኦት ሐ/ ውህደት መ/ አንድነት

36. «ሰርቶ እንደ መብላት <u>አንጀቱን ቋጥሮ</u> ይውላል » የተሰመረበት ሀረግ ትርጉም ---------- ነው ?

ሀ/ ተርቦ ለ/ ተሰብስቦ ሐ/ ተበድሮ መ/ ከስቶ

37. ከሚከተሉት ውስጥ ትልቁ የቋንቋ መዋቅር የሆነው የቱ ነው ?

ሀ/ድምፅ ለ/ ዓ. ነገር ሐ/ ድርሰት መ/ አንቀፅ

38. «ወደቀ» ብሎ «ተነሳ» ካለ «አያሌ»ብሎ -------ይላል

ሀ/ ጥቂት ለ/ ብዙ ሐ/ እሩቅ መ/ ቅርብ

39. «ይህንን ፈተና ለማለፍ ከነበረው ጉጉት የተነሳ <u>ወጥሮ</u> ነው ያጠናው»የሚለው ዓ.ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺው ምንድን ነው

ሀ/ ደክሞ ለ/ተዘርግቶ ሐ/ ተግቶ መ/ አክርሮ

40. የሳር ውስጥ መንገድ ይመስላል ወገቡ

መች ያስታውቃል ርሀብ ጥጋቡ። ይህ ቃላዊ ግጥም የሚገልፅው ምን ዓይነት ሰው ነው?

ሀ/ ሸንቃጣነስ/ አይነግቡን ሐ/ለግላግን መ/ ለስላሳን

41. ሁለት የተለያዩ ቃላት አንድ ላይ በመሆን የሚመሰርቱት አዲስ ቃል --------ይባላል ።

ሀ/ ኢ-ተዘውታ ቃል ለ/ ተዘውታሪ ቃል ሐ/ ዋና ቃል መ/ ድርብ ቃል

42. የንግግር ሂደት መመርያ ሀሳቦች ተዘበራርቀው ተፅፈዋል ፤ መመርያዎች በየትኛው ቅደም ተከተል ይፃፋል ።

ሀ/ ንግግር ሳቢና ማራኪ አድርጎ ማቅረብ

ለ/ ለተጠቁት ጥያቄዎች ገለፃ መስጠትና ማጠቃለል

ሐ/ በንግግር መጨረሻ ምስጋና ማቅረብ

መ/ የንግግር አላማ ማስተዋወቅ

ሀ/ ሐ፣ መ፣ ሀ፣ ለ ለ/ ሀ፣ መ፣ ሐ፣ ለ

ሐ/ መ፣ ለ፣ ሀ፣ ሐ መ/ መ፣ ሀ፣ ለ፣ ሐ፣

43. ከሚከተሉት ቃላት መካከል ልዩ የሆነው የቱ ነው

ሀ/ ጥንድ ለ/ ሌጣ ሐ/ ብቸኛ መ/ ነጠላ

44. <u>ሳር ቅጠሉ</u>ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ተመሳሳይ ፍቺ የሚሆነው የትኛው ነው።

ሀ/ ሁሉም ሰው ለ/ ጫካና ስሩ ሐ/ አጎት የሚነድ መ/ ሳር ሁሉ

45. «መሠረት ወደ ቤቷ እየሄደች ነው» በዚህ ዓ.ነገር ውስጥ የምናገኘው የጊዜ ዓይነት የትኛው ነው?

ሀ/ የሀላፊ ጊዜ ለ/ የአሁን ግዜ ሐ/ የትንቢት ጊዜ መ/ የቅርብ ሀላፊ ጊዜ

46. ከሚከተሉት መካከል በንባብ ጊዜ እንቅፋት ያልሆነው የቱ ነው

ሀ/ እያጉተመተሙ ማንባብ ለ/ ድምፅ ሳያሰሙ ማንበብ

ሐ/ በጣት እየጠቆሙ ማንበብ መ/ ቃላትን እየደገሙ ማንበብ

47. «ቤት» ብለን «አብያት» ብንል «ልብስ» ብለን ---------- እንላለን ።

ሀ/ ልብሶች ለ/ አልባስ ሐ/ መልበስ መ/ አልባሳት

48. ከሚከተሉት መካከል አዳምጦ ለመረዳት እንቅፋት የማይሆነው የትኛው ተግባር ነው?

ሀ/ ለንግግሩ ሳይሆን ለተናገረው ትኩረት መስጠት

ለ/ ለንግግሩ ትኩረት አለማድረግ

ሐ/ ሃሳብን ሰብስቦ በትኩረት ማዳመጥ

መ/ የጆሮ እመም

49. ሁለት እና ከዛ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል በተለያየ ርዕስ ጉዳይ ላይ የሚያደርጉት ምልልስ ---------- ይባላል

ሀ/ ልቦለድ ለ/ ጭውውት ሐ/ ትረካ መ/ ክርክር

50. ⊠ ይህ ምልክት ከሚከተሉት የትኛውን ይገልፃል

ሀ/ የአንቀፅ ሀይለ ቃል መጨረሻ መሆኑን

ለ/ የአንቀስ ሀይለ ቃል መካከል መሆኑን

ሐ/ የአንቀስ ሀይለ ቃል መጀመርያ መሆኑን

መ/ የአንቀስ ሀይለ ቃል መነሻ እናመድረሻ መሆኑን

51. ከሚከተሉት ዓ.ነገሮች ውስጥ እንጀራ የሚለው ቃል በተለየ አውድ የገባው ቤትኛው ነው

ሀ/ እናቴ እንጀራ ጋገረች ለ/ ምሳዬን እንጀራ በወጥ በላሁ

መ/ የምለፋው ለእንጀራ ነው ሐ/ የሚሸጥ እንጀራ አልወድም

<u>መመርያ ሶስት</u> ከጥያቄ ቁጥር 52 እስከ 55 ድረስ ያሉት የቅኔ ጥያቄዎች ናቸው ከተሰጡት አማራጮች ወርቀን (ምስጥራዊፍቺውን) ያየዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ

52. አዋዜው በዛፍ ምላስህን ተኮሰው

አነካከቶ መብላት አታውቅም እንደሰው

ሀ/ በመጠኑ እያጠቀስክ መብላት አታውቅም

ለ/ ከዚያም ከዚያም እየራመዱ መብላት አታውቅም

ሐ/ ከሰው እየተጣሉ መበልጸግ አታውቅም

መ/ ሰውና ሰው አጣልቶ መኖር አታውቅም

53. ቤታችን ተሰርቶ በመንታ መንገድ

እናያለን ሁሉን ሲመጣ ሲወርድ

ሀ/ አላፊ አግዳሚውን እናያለን ለ/ ወጪ ወራጁን እናያለን

ሐ/ የሚሾም የሚሻረውን እናያለን መ/ የሚመረቅ የሚረገመውን እናያለን

54. ሽማግ ሁል ጊዜ እለብስ የለም ወይ

ብርቅ መስሎ ታየኝ ጥበብ ለብሰው ባይ።

ሀ/ በእውቀት በልፃገው ባይ ተገረምኩ ሐ/ ጥበብ በጥበብ የሆነ ልብስ ለብሰው ባይ ተደነቅሁ

ለ/ በጥበብ ያማረ ነጠላ ለብሰው ባይ ብርቅ ሆነብኝ መ/ ሽማ መልበስ እንደማያስገርም ተገነዘብሁ

55. ስጋ እበላ ብዬ የቆረጥኩትን

ላሳያችሁ መጣሁ እኔማ ጣቴን

ሀ/ ስጋ መብላት ችግር ነው ለ/ ችጋር ይዞኛል

ሐ/ ስጋ ሲበላ ላሳያችሁ መ/ ስጋ ለበላ ጣቴን ቆረጥሁ

<u>መመርያ አራት</u> ከ 56 እስከ 60 ድረስ ያሉትን ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ግጥም ላይ የተመሰረቱ ናቸው ግጥሙን በማስተዋል ከነባብችሁ በኋላ ለእያንዳንዱ ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጮች መካከል ተገቢውን መልስ ስጡ።

ሞትና ሰውነት ሁሌም ይነቃሉ

ነፍስና ነፍስ ግን ወቅት ይጠብቃሉ

ሁሌ ሀያው መሆን አከተመ በቃ

የኛ ሕያውነት ሆኗል በፈረቃ

ምንጭ፦ ስብስብ ግጥሞች

በዕውቀቱ ስዩም

2001 ዓ.ም

56. ግጥሙ በራብዕ የሚጨርሱ ስንት ስንኞች አሉት

ሀ/ አራት ለ/ ሁለት ሐ/ አንድ መ/ ሶስት

57. የግጥሙ ሶስተኛ ስንኝ መድረሻ ሀረጉ የቱ ነው

ሀ/ ሁሉም ህያው ለ/ የእና ህያውነት ሐ/ አከተመ በቃ መ/ ሁሉም ይነቃሉ

58. ግጥሙ ስንት ስንኞችና ስንት ሀረጎች አሉት

ሀ/ አራት ሰንኝ ስምንት ሀረጎች ለ/ ስምንት ስንኞች አስራ ስድስት ሀረጎች ሐ/ ስምንት ሰንኞች አራት ሀረጎች መ/ ሁለት ስንኞች አራት ሀረጎች

59. በግጥሙ ውስጥ ወቅት (ጊዜ) እንደሚጠብቁ የተገለፁት እነማናቸው

ሀ/ ሞትና ሰውነት ለ/ ህይወትና ፈረቃ ሐ/ ነፍስና ነፍስ መ/ ሁሉም ናቸው

60. ከላይ ለቀረበው ግጥም ዕርስ ሊሆን የሚችለው

ሀ/ ህይወት ለ/ ጊዜያዊነት ሐ/ ጨረቃ መ/ ፈረቃ